# ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

## የኅዳር ወር ሦስተኛ ሰንበት

ከኅዳር ፯ እስከ ታኅሣስ ፯ ወይም ፲፫ አስተምህሮ ይባላል። በዚህ ቀን የሚዘመረው መዝሙር በክብረ ሰንበት ላይ የተመሰረተ ነው።

### የዕለቱ ምስባክ

ኵሉ ዘፈቀደ ገብረ እግዚአብሔር
በሰማይኒ ወበምድርኒ
በባህርኒ ወበኵሉ ቀላያት

በሰማይና በምድር በባህርና በጥልቆች ሁሉ
እግዚአብሔር የሚወደውን ሁሉ አደረገ።

መዝ ፩፻፴፬፥፮

ወንጌል፥ ዮሐንስ ፭፥፲፯-፳፫
ቅዳሴ፥ (ዘአትናቴዎስ) የአትናቴዎስ ቅዳሴ

### የዕለቱ የቅዱስ ያሬድ መዝሙር ርዕስ

ሎቱ ስብሐት ወሎቱ አኮቴት ለዘቀደሳ ለሰንበት
(ሰንበትን ለቀደሰ ለእርሱ ፍጹም ምስጋና ይገባዋል።)

### በቅዳሴ ሰዓት የሚነበቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች

| | ንባብ | አንባቢ |
|---|---|---|
| 1 | ቆላ ፩፥፲፪ እስከ ፍጻሜ | ዲያቆን (ገባሬ ሰናዩ) |
| 2 | ፩ኛ ጴጥ ፩፥፲፫-፳፩ | ዲያቆን (ንፍቅ ዲ.) |
| 3 | የሐዋ ሥራ ፲፱፥፳፩ እስከ ፍጻሜ | ረዳቱ ቄስ (ንፍቅ ካህን) |

### የዕለቱ ትምህርት

**«ሁሉ ለእርሱ በእርሱ ተፈጥሯል»**
ቈላ ፩፥፲፮

ቅዱስ ጳውሎስ ለቆላስያስ ሰዎች በላከው መልእክቱ ዛሬ በቅዳሴ ጊዜ ሲነበብ እንደሰማነው ሁሉ በኢየሱስ ክርስቶስ ስልጣን፣ ቃልነት፣ ፈጣሪነት ለእርሱ ክብር ተፈጠረ። በሰማይ ያሉ ሊቃነ መናብርት ስልጣናት ኃይላት ሁሉ በእርሱ መለኮታዊ ኃይል ተፈጥረዋልና። እርሱ የፍጥረት ሁሉ ገዢ ነው ብሎ አስተማረን።

ጌታችንም በወንጌል አባቴ እስከ አሁን ይሰራል እኔም እሰራለሁ ብሎ አሁንም ዓለምን በመመገብ በመምራት ላይ መሆኑን አስተማረን (ዮሐ ፭፥፲፯-፲፰)። ዮሐንስም በወንጌል «ወኵሉ ቦቱ ኮነ ወዘእንበሌሁሰ አልቦ ዘኮነ ወኢ.ምንትኒ (ሁሉ በእርሱ ሆነ ያለ እርሱም የሆነ ምንም ምን ነገር የለም)» ብሎ ሁሉ በአምላካዊ ቃል መፈጠሩን አስተማረን። አዎን ሁሉም በእርሱ ክሂል ተፈጥሮአል በጥንተ ተፈጥሮ ብቻ አይደለም በአዲስ ተፈጥሮም ሁሉ በኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ተፈጥሮአል። ያም ለእርሱ ክብር ለእርሱ ምስጋና ይቆም ዘንድ ነው።

ሁሉን በሁሉ ለሚገዛ ሁሉን በሁሉ ለሚሰራ በሰማይም ሆነ በምድር የወደደውን ለሚያደርግ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር ... አሜን።

